## መጽሐፍ ቅዱስ ለህፃናት
### አቅራቢዎች

# የገበሬው ምሳሌ




ጸሐፊው: Edward Hughes
ምሣሌ አቅራቢው: M. Maillot; Lazarus
ያሻሸለው (አሻሽሎ የጻፈው):
E. Frischbutter; Sarah S.
የተተረጎመው: Abel Eshetu
Alastair Paterson
አዘጋጁ: Bible for Children
www.M1914.org

BFC
PO Box 3
Winnipeg, MB R3C 2G1
Canada



©2020 Bible for Children, Inc.
ፈቃድ፡- ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ማባዛት ወይም ማተም ይቻላል ነገር ግን ይህ መሆን የሚችለው ለሽያጭ ካላቀረባችሁ ብቻ ነው።




በዚያን ቀን ኢየሱስ በባሕር አጠገብ ተቀመጠ፤ብዙ ሰዎች ወደ እርሱ ተሰበሰቡ፥ሕዝቡም ሁሉ በወደቡ አጠገብ ቆመው ነበር።

ምን ሊላቸው ይሆን?




እርሱም በጀልባ ገብቶ ተቀመጠ። እርሱ ሕዝቡን፣ ሕዝቡም እርሱን በደንብ ማየትና መደማመጥ ይችላሉ።
3


በምሳሌም ብዙ ነገራቸው፣ ስለእግዚአብሔር አስተማራቸው።
4


እንዲህም አላቸው፦ እነሆ፥ ዘሪ ሊዘራ ወጣ። ይገርማል! የኢየሱስ ምሳሌዎች ልክ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮች በስዕል ሲቀርቡ አይነት ነው።
5


ሰዎቹም ገበሬውን በአእምሮአቸው መሳል ይችላሉ።
6


እርሱም ሲዘራ አንዳንዱ በመንገድ ዳር ወደቀ፥ ወፎችም መጥተው በሉት።
7


ሌላውም ብዙ መሬት በሌለበት በድንጋያማ መሬት ላይ ወደቀ፤ ጥልቅ መሬትም ስላልነበረው ወዲያው በቀለ፥ ፀሐይ በወጣ ጊዜ ግን ጠወለገ፥ ሥርም ስላልነበረው ደረቀ።
8


ሌላውም በእሾህ መካከል ወደቀ፥
እሾህም ወጣና አነቀው። የፀሐይ
ብርሃንና ዝናብ ማግኘት ስላልቻለ
ፍሬ ማፍራት አልቻለም።
9


ሌላውም በመልካም መሬት ወደቀ፤ አንዱም
መቶ፥ አንዱም ስድሳ፥ አንዱም ሠላሳ ፍሬ
ሰጠ። ገበሬው በጣም ደስ የሚለው ይመስላል።
10


ደቀ መዛሙርቱም ወደ ኢየሱስ ቀርበው። ለምን በምሳሌ
ትነግራቸዋለህ? አሉት።
11


ኢየሱስም ምሳሌዎች ሰዎች እግዚአብሔርን ከልባቸው የሚወዱ
ከሆ ስለእርሱ እንዲያውቁ ይረዳቸዋል። እግዚአብሔርን ከልባቸው
የማይወዱ ሰዎች ምሳሌዎችን ላይረዱ ይችላሉ።
12


ኢየሱስም ምሳሌውን አብራራ። ዘሩ
የእግዚአብሔር ቃል ነው፡- አለ። በመንገድ
ዳርም ያሉት የሚሰሙ ናቸው፤ ከሰሙ በኋላ ዲያብሎስ
ቃሉን አምነው
እንዳይድኑ
እንዲረሱትም
ያደርጋል።
ስለዚህ
ቃሉን
አያስተውሉም፤
አላቸው።
13


በድንጋይ ላይም ያሉት ሲሰሙ ቃሉን በደስታ
የሚቀበሉ ናቸው፤ እነርሱም ለጊዜው ብቻ
ያምናሉ እንጂ ሌላ ሰው ሲያሾፍባቸው
ወይንም ችግር ሲደርስባቸው
ቃሉን ይዘነጉና እግዚአብሔርን
ይተዋሉ። አላቸው።
14

በድንጋይ ላይ ያሉት ደስ እያላቸው እግዚአብሔርን የሚከተሉ ነበሩ፣ ነገር ግን መፅናት ባለመቻላቸው የእግዚአብሔርን ቃል መታዘዝ ያቆሙ ናቸው። እነዚህ ከእግዚአብሔር ይልቅ ጓደኛን፣ዘመድን እና ሌሎችን የሚያስቀድሙ ናቸው። ከምንም ነገር በላይ እግዚአብሔር ይቀድማል ማለት አልቻሉም። ያሳዝናል!



15

በእሾህ መካከል የተዘራውም ቃሉን የሚሰሙት ናቸው፥ የዚህ ዓለም ጭንቀትና ገንዘብን መውደድ ቃሉ በሕይወታቸው እንዳይሰራ ያደርጋል፥ ስለዚህም ፍሬ አያፈራም። ሁልጊዜ ብዙ ገንዘብ ለማግኘት ስለሚሯሯጡ እግዚአብሔርን ከሕይወታቸው ያስወጡታል።



16

በመልካም መሬት ላይ የወደቀው ትርጉም እነርሱ በመልካምና በበጎ ልብ ቃሉን ሰምተው በሕይወታቸው የተለወጡት ናቸው። እነኚህ ሁልጊዜ እግዚአብሔርን የሚፈሩና የሚያገለግሉ ናቸው።



17

ሕዝቡ ከኢየሱስ መለየት አልፈለገም። ብዙዎች እግዚአብሔርን ለማክበርና ደስ ለማሰኘት ፈለጉ። የኢየሱስ ምሳሌዎች እንዴት እግዚአብሔርን መታዘዝ እንዳለባቸው እንዲያስተውሉ ረዳቸው።



18

የገበሬው ምሳሌ

ይህ ታሪክ የሚገኘው የእግዚአብሔር ቃል በሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ

ማቴዎስ ወንጌል ምዕ. 13

“የቃልህ ፍቺ ያበራል.”
መዝሙረ ዳዊት 119:130

19

# መጨረሻ

43 60

20

ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ የሚያስተምረን ግሩም ስለሆነው አምላካችን እግዚአብሔር እኛን በመፍጠሩ እሱን እንድታውቀው ነው።

እግዚአብሔር “ኃጢአት” ብሎ የሚጠራውን ክፉ ነገር እንዳደረግን ያውቀዋል። የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው ነገር ግን እግዚአብሔር በጣም ስለወደደን አንዱንና ብቸኛው ልጁን ለቀራኒዮ መስቀል ሞት አሣልፎ በመሥጠት እንዲሞትና የኃጢአታችንን ዋጋ በእኛ ምትክ በመሞት እንዲከፍል አደረገው። ኢየሱስ ከሞት ከተነሣ በኋላ በምድር ላይ ቆይቶ ወደ ሠማይ ወደ አባቱ አረገ! ያላመንን እኛም በኢየሱስ አዳኝት ብናምን እና ኃጢአታችንን ይቅር እንዲል ብለምነው ይቅር ይለናል። ደግሞም ያደርገዋል። እሱም በእኛ ውስጥ ይኖራል፤ እኛም በእርሱ ውስጥ ለዘላለም እንኖራለን አሜን።

ይህ እውነት እንደሆነ ካመናችሁ፣ እግዚአብሔርን እንዲህ በሉት
ጌታ ኢየሱስ ሆይ አንተ አምላክ እንደሆንክ አምናለሁ ነገር ግን ለእኔ ኃጢአት ለመሞት ስትል ሰው ሆንህ አሁን ደግሞ ህያው ነህ። እባክህ ወደ ህይወቴ ግባ ኃጢአቴን ይቅር በል በዚህም አዲስ ህይወት አሁን ይኖረኛል አንድ ቀን ከአንተ ጋር ለዘልዓለም ለመኖር ወደ አንተ እመጣለሁ። ለአንተ እንድኖርና እንደ ልጅ እንድታዘዝልህ እርዳኝ። አሜን።

በየዕለቱ መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ ከእግዚአብሄር ጋር ተነጋገር! የሐ. 3.16